ከ1935 እስከ 1940 የጣሊያን ወረራ በኢትዮጵያና የሴት አርበኞች

We look back in admiration and sorrow to all that pain, to all that fervour. We particularly remember that woman who presented herself to Us during the inspection we made in the Ogaden, in the early times of the war. She wore a cartridge belt and held tight an Italian rifle. These weapons had formerly belonged to the man who killed her husband in front of her eyes and then waded into her to abuse her. The whole Ethiopia was in that woman.

(H.I.M. Haile Sellassie I, Emperor of Ethiopia, *L'invasion de l'Ethiopie,* chapter 12).

የአገራችን የኢትዮጵያ ሴቶች ጦር ሚና በቂ አድርጎ ለመግለፅ በጦር ሜዳ ያልተሣተፉትንም ማንኛዉንም ሴቶች ማጠቃለል ያስፈልጋል። ምክንያቱም አብዛኞቹ ሴቶች በኢትዮጵያ የመከላከያ ጦር ግንባር ላይ ባይሳተፉም ለጦሩ ሞራል በመስጠት (በፉከራ በዘፈን) በአብዛኛው በአገራችን የተካሄደውን ጦርነት በድል እንዲወጣ ስንቅ ( አገልግል ) በማዘጋጀት፣ ውሀ ከወንዝ ቀድቶ በማቅረብ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች ከጦርነት ወደ ጦርነት ለሚጓዘው የንጉስ ጦር ለድል እንዲበቃ ትልቅ ሚና በመጫወታቸው ክብር ሊሰጣቸው ይገባል።

አንድ የታወቀ ተጓዥ እና ፀሐፊ James Bruce በአንድ ወቅት ስለነዚህ ሴቶች በጦርነት ጊዜ ያደረጉትን አስተዋፅኦ እንደገለፀው (እንዳሰመረበት ) "በዚህ አለም ማንም ሴት እንደ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ቀን ከለሊት ሳይለዩ፣ ሳይደክሙ፣ ሳይሰለቹ ጦሩ ወደጉዞ ይዞት የሚሄደዉን ስንቅ በማዘጋጀት ዉሀ በእንስራ ተሸክመዉ በማጓጓዝ በማቅረብ የሚሠሩ ጠንካራ ብርቱ ሴቶች ናቸው ሲል ገልፆታል። በተጨማሪም በዕለት ዕልት ኑሮ ካልተለወጠሩ፤ መንገድ በማፅዳት፣ የተጎዱትን አርበኞች የህክምና እርዳት በመስጠት ሲሳተፉ ታይተዋል። በዚህ የስነ ልቦና ስሜትም ልእልት ፀሐይ ሀይለ ስላሴ በጣሊያንና ኢትዮጵያ ጦርነት ጊዜ በማናቸዉም ክፍል ዉስጥ ሴቶችን በማስተባበር ለቁስለኞች ፋሻን በማድርግ ፤ልብስ በወቅቱ እንዲደርስ፤ ከጠላት የሚወረወረውን መርዝ እንዴት አድርጎ መከላከል እንደሚቻል ስታሳይና ስታስተምር ታይቷል።በተጨማሪም ልዕልት ፀሐይ ሀይለ ስላሴ ቋንቋን በማስተርጎም ለሀገሯ ትልቅ አስተዋፅዎ ያደረገች ልዕልት ነች ።

ስለዚህ ሁልጊዜ ማሰብና ማስታወስ ሊኖርብን የሚገባው ቀደም ብሎም ቢሆን በአድው ድል ላይ ሴቶች ምን ያህል ለሠራዊቱ በተለያየ መንገድ ለጦር መከላከያዉ ትልቅ አስተዋፅኦ በማድረጋቸዉ ከውጭ ለመጣ ጠላት ሳይሸነፉ ለአመት ሳይሆን ለብዙ ዘመነ አመታት ክብርና ነፃነት ሀገራችን እንዲኖራት አድርገዋል።

## ሴት አርበኞች

ብዙ ሴት እርበኞች የጣሊያንን ወረራ ለማክሸፍ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል። በዚያ ወቅት በወ/ሮ ሸዋ ረገድ በኋላም በልዕልት ተናኘወርቅ ሀይለስላሴ ተቋቁሞ የነበረ ነፃ አገልግሎት የሚሰጥ ማህበር ነበር። በዚህ ስር የነበሩ አርበኞችም በጦርነቱ ግንባር በመሠለፍ ተዋግተዋል ከነዚህም ውስጥ ወ/ሮ ሸዋ ረገድ፣ ወ/ሮ ከበቡሽ፣ ወ/ሮ ፋንታዬ እናም ሌሎች ብዙ ስማቸዉ ያልተጠቃሱ ሴት ታጣቂ አርበኞች ነበሩ። አብዛኛዉ የሴት አርበኞች ልዩ ያረጋቸው የነበረው የጠላት ጦር መቃረቡን ለአርበኞች በጥሩንባ ( እንቢልታ) በመንፋት የሚያሳዉቁ ሴት አርበኞች እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል። በተጨማሪ ከአይሮፐላን የሚወረወረዉን ፈንጂ ከምንም ሳይቆጥሩ በከፍተኛ ቦታ በመደበቅ የጠላት ጦር በሚያልፍበት ትላልቅ የድንጋይ ናዳ በመልቀቅ፣ መንገድ በመዝጋት ይከላከሉ የነበሩ እና መሳርያዎችን አፀዳድተው የማቅረብ አስተዋፅኦ ያረጉ የነበሩ ሴት አርበኞች እንደነበሩ መረዳት እንችላለን። እንደ ወ/ሮ ፅጌ መንገሻ ያሉ አርበኞች የቆሰሉ ወገኖችን በህክምና ይረዱ እንደነበር ይታወቃል።

የታሪክ ፀሐፊዎቹ እንዳስቀመጡትና እንደሚገምቱት በጣም ብዙ ሴቶችም የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዉበታል የታሪኩ ፀሐፊ Andrew Hilton The Ethiopian Patriots "Forgotten Voices of the Italo-Abyssinian war 1935-41 በሚለው መፅሐፉ ላይ በሕይወት የሚገኙትን የሁለት ሴት አርበኞች ቃለ መጠይቅ ያረገዉን ለምስክርነት አቅርቤዋለሁ።

ቆራጥ አርበኞቹ ወ/ሮ አለሚቱ መኮንን እና ወ/ሮ ዘነበች ወ/የስ ሲባሉ ሁለቱም የ80 ዓመት እድሜ ያላቸው አዛውንቶች ናቸዉ።

ወ/ሮ አለሚቱ መኮንን በወረራዉ ጊዜ ምንም እንኳን የ15 ዓመት ዕድሚያቸዉን ለመያዝ ቢዘጋጁም ብዙ ነገር የሚያዉቁና የተገነዘቡ ሴት ናቸዉ ። በዚያ ወቅት የ15 ዓመት ዕድሜ ያለው ማንኛዉም ወንድም ሆነ ሴት ተኩሶ ለመግደል ብቃት አለው ተብሎ ስለሚገመት እኔም ቤተሰቦቼ ገና የአስር ዓመት ልጅ እያለሁ አነጣጥሮ መተኮስ ሰላስተማሩኝ ብዙም አልተቸገርኩም። አያቴ በአድዋ ጦርነት አባቴና ወንድሞቼ በጣሊያን ወረራ ጊዜ በቀደምትነት በሠለጠነ መሣሪያ ሳይሆን ባላቸው የቆየ ጠመንጃ ፤ፉቺሌ(Fucill) በዚያን ግዜ ይታወቅ የነበረዉ ናስ ማስር( Nas Masr) ስናድር እና ውጅግራ በመያዝ ነበር ከጠላት ጋር ግብ ግብ የገጥሙት(ይዋጉ) የነበሩት እና ህይወታቸዉን ንብረታቸዉን ለኢትዮጵያ አገራቸው መሰዋትነት የከፈሉት ። እኔም የነሱን መርህ በመከተል እራሴ በቀደምተኝነት እንዳዘጋጅ ያደረገኝ። በተጨማሪ የወንድሜ በጠላት እጅ መውደቅና በጥይት ተደብድቦ ከመገደሉ ሌላ ጥርሶቹን አውልቀዉ ሬሳዉን ከሶስት ቀን በኋላ ገደል ውስጥ ጥለውት በማግኘታችን ነዉ። እንደ ጦር ህግ ቢሆን ኖሮ ተይዞ ለፍርድ ይቅርብ ነበር እንጂ እንደነሰሳ የትም አይጣልም ነበር።

እነዚህ ሁኔታዎች እና የ 17ቤተሰቦቼ እልቂት ሁሉን ነገር ትቼው ወደ በረሀ በመግባት ትግሌን ከወንዶ ገጠም (ሰሚ ማርያም) ተብላ በምትጠራው በጣም በምትታወቅ ቦታ በቤጌምድር ዉስጥ ስትገኝ ለአባይ በጣም የቀረበ ቦታ ላይ ነው። ይቺ ቦታ በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ ጣሊያኖች በግራና በቀኝ ጦራቸዉን ያሰፈሩባት ነበረች። በዚች ስፍራ የአርበኞችን ጦር የሚመሩት ግራዝማች ተድላና ግራዝማች ገብሬም በጠላት የተገደሉባት ቦታ ነበረች። የምሳተፍበት ጦር ለመበታተን ቢገደድም እኔ ግን ከሌሎች አርበኞች ጋር በመቀላቀል ትግሉን ቀጠልኩኝ። በርግጥ ይህን ስል እንደ ጠላት በሰለጠነ መሣሪያዎች መዋጋት ባንችልም ባለን የአገር ፍቅር እና ቆራጥ ውሳኔ በመነሳሳት በአለን መሳሪያ በዉጊያው ተሳታፊ ሆነናል። ከማስታውሰው አንድ ጊዜ የጠላትን የራሽን ( ዕቃ) ማጓጓዣ አይሮፕላን ተኩሰን በመጣል የሠለጠኑ የጠላት ጦር መሰርያ፣ ዳቦ፣ ማርማራታ የማርከንበት ወቅትና በሰለጠነ መሳሪያ እየታገዝን ለድል የበቃንበት ሁኔታም ነበሩ።

በዚያን ጊዜ ሌላው ሳልጠቅሰው ማለፍ የማልፈገው የሬዲዮ መገናኛ ባለመኖሩ ከሌሎች ራቅ ካሉ አርበኞች ጋር የደብዳቤ ልውውጥ እናረግ የነበረው በእንጨት ዱላ (መቃ) ውስጥ መልክቱን በመከተት መልክቱ ማንም በማይጠረጥር መንገድ ለሌሎች አርበኞች እንዲደርስ እናደርግ ነበር። እንዲሁም የአንዱ አገር አርበኛ ከሌላው አርበኛ ጋር በጠላት ላይ ሊደረግ የሚገባዉን እንነጋገር ነበር። የጦር መሳሪያ ሌሎች ሌሎችንም እርዳታዎች እንለዋወጥ ነበር። ከጎንደር ጥጥ ወደ ጎጃም ተልኮ ለአርበኞች የሚለብሱት ልብስ ይሰራ ነበር። ሕዝቡም ውሀ ብንጠይቅ ወተት ሰጥቶ በሚያስፈልገዉ ሁሉ እንክብካቤ እድርጎልናል።

ሌላው ትልቁ ሳልልው ማለፍ የማልፈልገው ብዙ ሰው እንደሚገምተው ንጉሣችን አገር ሸሽተው እንደለቀቁ ተደርጎ እስከዛሬ ሲነገር እሰማለሁ ። እውነታው ግን እንደዚህ አይደለም። በሀገር ወዳድ ሰዎችና በእኛ አርበኖች ግፊት ወደውጭ ሀገር ወጥተው የሀገራችንን የጣሊያን የግፍ ወረራ ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅ መዉጣት እንዳለባቸው በአደረግነው ግፊት ነው። ከንጉሳችን በማንኛውም ግዜ የማበረታቻ መልዕክት በሰውም ይሁን በደብዳቤ በየግዜው ይደርሰን ነበር። በመጨረሻውም ግዜ ወደድል በምንቃረብብት ወቅት ከእንግሊዝ ጦር ጋር ሲመለሱ የጣሊያን ፋሽሽት ጦር ከውጭ የጦር ሀይል መምጣቱን ሲረዳ በጣና ሀይቅ ውስጥ ብዛት ያላው ወርቅና ብር እንዲሁም የሰዎች አስከሬን በደብረ ታቦር በጢስ አባይ እንዲሁም በለሎች ስፍራዎች የጣለዉን አግኝተናል። እስካሁን የአላውቅነው የተገኘው አፅም ሁኔታ ነው ጥሊያኖቹ የሚበሉት የከብት ስጋ ቢሆንም፤ የተገኘው አፅም በጨካኙ ፋሽሽት የተጨፉ ሴቶችን ጭምር ነው ።

በመጨረሻም በራሴና በሌሎች አርበኞች ስም ልል የምችለው፤ ሁላችንም ታሪክ ሰራን፣አየን ምንም እንኳን የህይወትን አስከፊ ገፅታዉን እንድናይ ብንገደድም አብዛኞቻችን ከአባቶቻች እና ከእናቶቻችን የወረስነው ቆራጥ ትግልና እምነት በምንም አይነት ምክንያት ሀገራችንን በባእድ (በጠላት) እጅ አሳልፍ ሰጥቶ በነጭ መመራትና መገዛትን አለመፈለግ ነበር። ይህን በማድረጋችን ኩራት ይሰማናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሁላችንም በህይወት ባንኖርም ያለነውም በዕድሜ ገፋ በማለታችን የእለት እለት እንቅስቃሴ ዉስጥ መሳተፍ ባንችልም ተስፋችንና ምኞታችን ለአዲሱ ትዉልድ እንደዚህ እያልን በአደራ እንገልጻለን፤ ሀገራችን ኢትዮጵያን ሁልጊዜም ከጠላት ነፃ አድርጋችሁ እንድትጠብቋት። እኛ ለእናንተ ውድ ሀገራችንን ያስረክብናት ተርበን፣ተዋርደን፣ ተገድለን፣በቆዳ በሽታ ተለክፈን ለጠላት አንሸነፍም በማለት ስለሆነ እናንተም ይኽንን መጠበቅ አለባችሁ አደራም እላለሁ።

ሌላ እንዳትረሱ የምለው እኛ ኢትዮጵያኖች የራሳችን የሆነዉን ለሌላው አንሰጥም የሌሎችንም አንፈልግም። ውዷ ሀገራችንን የውጭ ጠላት መጥቶ በድፍረት ሲወራት እንቢ በማለት በቆራጥነት ታግለን አሸንፈናል። ይኸውም የተገኘው በትግል ብቻ ሳይሆን በሀይማኖታችን የፀናን በመሆናችን ነው። ያለ እምነታችን ይኽ ሁሉ ሀይል ከየትም አናጋኝም ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር አገሬን ትውልዴን እንዲጠብቅልኝ የሁልጊዜ ፀሎቴ ነው።

ሌላዋ ሴት አርበኛ ወ/ሮ ዘነበች ወ/ማርያም ይባላሉ የ80 ዓመት አዛዉንት ናቸው። የሀገር ፍቅር የተነሣሣብኝ ባለቤቴ ከማይጨው ጦርነት ድል አድርገው ከተመለሱ በኋላ ነው። ከዚያም በአምስት ዓመት የጣሊያን ወረራ መሳተፍ የጀመርኩት የ15 ዓመት እንዳለኝ ነው

ለጠላት መስገድና እጅ ላለመስጠት ያለኝ ፅናት ነው። ጠላት በአጭር ጊዜ በአካባቢዬ ቡልጋ ድረስ በመምጣት ቤቶችን፣ ከብቶችን፣ንብረቶችን በእሳት አወደመ። ይህን የፈፀመን ጠላት ለመዋጋት ወደጫካ በመሄድ ከአማፂያን ጋር ተቀላቀልኩ።

በአርበኝነት ያገለገለገልኩት ቀኛዝማች ለቅየለህ በሚመሩት ጦር ሰር በኋላም ራስ አበበ አረጋይ ጋር ነበር። የመዋጋት ልምድ አልነበረኝም። አማጽያን በአስተመሩኝ የተኩሶ መግደል ስልጠና እንጂ። አብዛኛው ሴት አርበኞች እንደኔው ነበሩ። ብዙም የጦር መሳሪ አልነበረንም ፤ መሳሪይ ያገኘነው መሳሪያ ካለው ላይ በመግዛት ነው ይህ ይካሄድ የነበረው በውስጥ አርበኞች አማካኝነት ነበር። መንግስት የነበረው መሣሪያ የተከፋፈለው በከተማው ላሉት ጦረኞች ነበር። በየጊዜው በማረከናቸው የጦር መሳሪያ የበለጠ በተሻሻለ መሳሪያ እየታገዝን ለመዋጋት ችለናል።

ትግላችንን የምናደርገው አንድ ቦታ በመሆን ሳይሆን ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ነበር። ከሌሎች አርበኞች ጋር እየተቃላቀልን ትልቅ ትግል አድርገናል። አንድ ጊዜ ካለሁበት ማለትም 50ኪ.ሜ በምስራቅ አዲስ አበባ፣ በደብረዘይት አጠገብ፣ ዝቋላ ተራራ ላይ በመቆየት የጣሊያንን ጦር እንዳይጠጋ ስንጠባበቅ ነበር። ውግያ በአካሄድኩባቸዉ ቦታዎች ጠላት በአየር ድብደባና በምድርም በከባድ የጦር መሳሪያ ወገኔን ያጠቃበትና እኛም ይህን ሁሉ በመቋቋም የጠላትን ሀይል በማድከም ወደከተማ የዘለቅንበት ጌዜም ነበር።

በተሳተፍኩበት ቦታዎች ላይ የአርበኝነቴን ግዴታ ብወጣም በተለይ የማልረሳው ዋሲል በተባላ ቦታ ላይ ሰላሳ የሚሆኑ አርበኞች ከጠላት ከሰማይ በተወረወረ ቦንብ ይገደላሉ ከአርበኞቹ አንዱ ስሙ እሸቱ እግሩ ላይ ተመትቶ ወድቆ አየሁት ይህ ጎበዝ አርበኛ የንጉሳችን የዘብ ጠባቂ ሆኖ ያገለግል እንደነበር ስለማውቅ በፍጥነት ሄጄ አንስቼ ከሱ እገዛ ጋር ባንዱ ትከሻዬ እሱን በሌላው ደግሞ ጠመንጃዬን ይዤ ወደተራራ አጠገብ በመውሰድ በመደበቅ ከጠላት እጅ እንዳይወድቅ አድርጊያለሁ። ሌላው የማስታውሰው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ስንጓጓዝ ለካ እኔ ቀድሜ ከጦሩ በመገንጠል ርቄ ተጉዤ ከጠላት ጦር መሀል በድንገት እገባለሁ። እዚህ ላይ ምን እንደሚሰማኝ ልትገምቱ ትችላላችሁ። እኔ ግን በፍጥነት በሩጫ ጥቅጥቅ ወደ አለው ከስሚ ወንዝ ( Kessem River ) አጠገብ ላምስት ቀን በመደበቅ ከጠላት እጅ በማምለጥ ከአርበኞች ጋር መቀላቀል ችያለሁ።

ስንቱ ይነገራል? በለት ዕለት የገጠመንን ላዉጋችሁ ብል ብዙ ጊዜ ይፈጃል። እንድትገነዘቡ የምፈልገው ጠላት አገራችንን አልመራትም፤ ያደረጉት አንዳንድ የታወቁ ቦታዎች ላይ በመስፈርና የመከላከያ ግንቦችን በማጠር ፣ ዙሪያዉን በመቆጣጠር እንጂ ይህ የሆነው አርበኞች በመከላከላቸው ነው። ስለዚህ የጣሊያን ጦር ያደረገው የተውሰኑ ከተማዎችን ከመቆጣጠር ሌላ ዘልቆ በመግባት ኢትዮጵያን በሙሉ ማስተዳደር አልተቻለውም።

ኢትዮጵያ የጀግኖች አገር ናት። ይኽን ስል የጣሊያን ፋሺሽቶች በመርዝ ጨርሰውናል፣ በቦንባቸው ገለውናል፣ በእሳት ከብቶታችንና ንብረቶቻችንን አቃጥለዋል፣ ከሁልም በላይ ታላላቅ መሪ አርበኞችን አጥተንበታል፣ ብዛቱ ሊገለፅ የማይችል ንፁህ ህዝብ እንደቅጠል እርግፎበታል። የህን ሁሉ ዛሬ እንደ ዛሬ አስታውሰዋለሁ ። ስለዚህ መጪው ትውልድ ውድ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ጠብቆ ለመጪው ትውልድ እንዲያስረክብ አደራዬ ነው ።

እንግዲህ እኔም በዕለቱ ከተገኙት ጣሊያኖች በተደጋጋሚ ሲነገር የነበረው በተጣለ መርዘኛ ጋዝ ያለቁት ወንድ ሴት፣ ህፃን ሽማግሌ፣ንብረት ሲታውስ ምን ያህል የሚያሳዝንና ከመወገዝ ወደኋላ የማያስብል፣ የማይፋቅ በአሁኑ ጊዜ በአለም አቅፍ የውጭ ፖሊሲያቸው “ ጣሊያን ደግ ሕዝብ “ ተብሎ እንዲታወቅ ( እንዲወራለት) ስላደረገው ኢትዮጵያን በወረረ ወቅት የፈፀመዉን ግፍ እና እልቂት መቼም እንዳይወገዝ አድርጎታል። አንድ ሌላ የታዘብኩት ነገር ቢኖር ጣሊያኖች በራሳቸው ሕዝብ ላይ ፋሺሽት ናዚ በፈፀመው ጭፍጨፋ በየጊዜው ሲያወሱ ፈፃሚዉን ተጠያቂ ሲያደርጉ እንሱ በአገራችን ላይ የፈፀሙትን ሰቅጣጭ ጭፍጨፋ ዞር ብለው ለአንዳፍታም እንዲያዩት አለማድረጋችን የእኛ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ቸልተኝነት ነው እላለሁ። “አንድ ጥሊያን አርበኛ በነጻነታቸው ቀን ምን ተሰማዎት ተብለው ሲጠየቁ “ በስሜ መጠራቴ “ ነው ትልቁ ደስታዮ ብለዋል።

Italians, good people? The unsolved question of the Ethiopian War and the italian colonialism.

Marina D'Ecclesiis, Radio Città Aperta

"Coming back on the Ethiopian war means today comparing with our actual abyss: with the legend of "italians, good people"; always useful in times of an aggressive foreign policy, with prejudices for the "others" that is the result of a coloialist past never criticized.

This is the theme of the conference held yesterday at the Physic Faculty, La Sapienza University, Rome:"Ethiopia 1935/1941: journey in the Italian dark heart",
The war in Ethiopia was one of the many shames of the fascist Italy, today forgotten. This war, conducted in the name of "civilization", hides many hard barbarities of the Italian army, as the use of mustard gas against civilians. This war has seen 760.000 victims and, as emphasized by Loredana Baglio from "Corrispondenze Metropolitanee", "[this war] has seen women as protagonists too, because of the violence and abuses perpetrate against them from the Italian invaders, lead by the legend of the "new fascist man": dominant, strong and superior". Therefore, the strength of the Ethiopian Resistance belongs even to them, to those women who suffered abuses but still kept bearing in everything their fathers and their brothers. Without them, the Resistance would have been, maybe, impossible, considering the armaments difference.

Today it's important remembering what happened in Ethiopia, because of the analogy with the actual Italian foreign policy: the fascist regime of Mussolini showed to the Italian people that the war in Ethiopia would have been a peaceful occupation. The Ethiopian man was represented as an inferior one to be civilized. To justify those racist conception, the regime used not only scientific theories, but even an obsessive propaganda that showed black men as slaves, primitives, letting enter in the Italian culture stereotypes: in fact, the Ethiopian war coincides with the period of greatest agreement to the regime by the Italians. Nowadays the situation is not so different: as underlined by the anthropologist Nancy Aluigi Nannini "our culture is soaked with colonial categories, especially in our language", and even today they talk about civilization and exporting democracy.

Moreover, the emphasis given in Italy to the theme of "security" with the help of the National press legalized every kind of discrimination against foreigners. Time ago, the USA journal "The Nation" accused Italy to be a racist nation, and the episodes of violence against immigrants are more and more frequent. So, this is the time for our nation to face with our past, to solve the present social plagues and to stop the neo-colonialism process of this new millennium.

Italiani brava gente? Il nodo irrisolto della Guerra d'Etiopia e del colonialismo italiano
Marina D'Ecclesiis, Radio Città Aperta.
"Tornare sulla guerra d'Etiopia oggi, vuol dire confrontarsi col nostro abisso attuale: con il mito degli "italiani brava gente"; sempre utile in tempi di politica estera aggressiva, con quei pregiudizi verso l'altro che sono anche il portato di un passato colonialista mai criticato". Questo il tema della conferenza-dibattito, "Etiopia 1935/1941: viaggio nel cuore di tenebra italiano", che si è tenuto ieri presso la facoltà di Fisica dell'Università La Sapienza di Roma.
La guerra d'Etiopia fu una delle tante vergogne dell'Italia fascista, oggi dimenticata. Una guerra portata avanti in nome della 'civiltà', che dietro nasconde le più gravi barbarie commesse dall'esercito italiano, come l'utilizzo di gas mortali contro la popolazione civile. Una guerra che conta 760.000 vittime e che, come sottolinea Loredana Baglio di Corrispondenze metropolitane, "ha visto come protagoniste anche le donne, costrette ai più atroci abusi da parte degli invasori, guidati dal mito del "nuovo uomo fascista": dominatore, forte e superiore rispetto all'altro sesso". Dunque, la forza della Resistenza etiope è attribuita anche a loro, a quelle donne che hanno subito abusi e che hanno continuato a supportare in tutto, i loro padri e fratelli patrioti. Senza di loro, la guerra di Resistenza, sarebbe stata probabilmente impraticabile, vista anche la disparità di armamenti.
Ricordare oggi quanto avvenuto in Etiopia è importante per le forti analogie con l'attuale politica estera italiana. Il regime fascista di Mussolini rappresentava al popolo italiano la guerra di Etiopia come un'occupazione pacifica. L'uomo etiope era rappresentato come un essere inferiore che in quanto tale andava civilizzato. Per giustificare queste concezioni fortemente razziste, il regime si servì non solo di teorie scientifiche ma anche di una propaganda ossessiva in cui gli uomini di colore erano rappresentati come servizievoli o primitivi, facendo penetrare nella cultura forti stereotipi:

la guerra d'Etiopia, infatti, coincide con il periodo di massimo consenso al regime tra il popolo italiano. Oggi la situazione non è molto diversa: come sottolinea l'antropologa Nancy Aluigi Nannini, "la nostra cultura è intrisa di categorie coloniali, presenti soprattutto nel nostro linguaggio", e ancora oggi si parla di popolazioni da civilizzare, e di esportazione della democrazia.

Moreover, the emphasis given in Italy to the theme of "security" with the help of the National press legalized every kind of discrimination against foreigners. Time ago, the USA journal "The Nation" accused Italy to be a racist nation, and the episodes of violence against immigrants are more and more frequent. So, this is the time for our nation to face with our past, to solve the present social plagues and to stop the neo-colonialism process of this new millennium.

Inoltre l'enfasi della destra italiana sul tema della "sicurezza" con l'aiuto della stampa nazionale ha legalizzato ogni tipo di discriminazione nei confronti di stranieri. Tempo fa addirittura il giornale statunitense "The Nation" ha accusato l'Italia di essere una nazione razzista, e gli episodi di violenza a danno di immigrati sono sempre più frequenti. Dunque, è il momento che la nostra nazione faccia i conti con il proprio passato per risolvere anche le piaghe sociali del presente e bloccare il processo di colonialismo del nuovo millennio.